# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዲያስፖራ ረቂቅ ፖሊሲ

## ለውይይት የቀረበ መነሻ ሀሳብ

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ህዳር 2004 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

# ማ ው ጫ

ርዕስ


**መግቢያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1**

**ክፍል አንድ**

**1. የዲያስፖራ ተሳትፎ ነባራዊ ሁኔታዎች ቅኝት . . . . . . . . . . . . . . . . .2**

**1.1.የዳያስፖራ ተሳትፎ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . 2**

**1.2.የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ተሳትፎ ቅኝት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3**

**2. የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፖሊሲ አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . 6**

**3. የዲያስፖራ ፖሊሲ ትርጉምና ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7**

**ክፍል ሁለት**

**4. የፖሊሲው መሰረታዊ መርሆዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8**

**4.1.ሴክተር አቀፋዊነት** (A sector Wide Approach . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

**4.2.ውጤታማነት** (A Safe Policy) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

**4.3.የሃብት አጠቃቀም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8**

**4.4.ተደጋጋፊነት** (Complementarities) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

**5. የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8**

**5.1.በውጭ ሚኖሩ ዜጎችን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ . . . . . . . . . . . . . . . 8**

**5.2.የኢንቨስትመንት፣ የንግድና ቱሪዝም ተሳትፎ ማጐልበት . . . . . . . . . . 10**

**5.2.1.ኢንቨስትመንት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10**

**5.2.2.ንግድና ቱሪዝም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .. 11**

**5.3.የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12**

**5.4.የውጭ ምንዛሪ ዕድገት ተሳትፎን ማሳደግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 13**

**5.5.ባህላዊ እሴቶችን ማዳበርና ገጽታ ግንባታን ማትጋት . . . . . . . . . . . . 14**

**5.6.በዲሞክራሲያዊ ሂደት ሚኖረውን ተሳትፎ ማሳደግ .. . . . . . . . . . . . . 14**

**5.7.የግብረ ሰናይና የልማት ማህበራትን ማትጋት . . . . . . . . . . . . . . . . 15**

**ክፍል ሶስት**

**6. የፖሊሲው ስትራቴጂዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .16**

**6.1.አስተማማኝ የመረጃ ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት . . . . . . . . . . . . . . 16**

**6.2.ለዳያስፖራው ተሳትፎ ዕውቅና መስጠት** (A ward and Recognition) . . . . 17

**6.3.የተደራጀ ተሳትፎ ማትጋት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17**

**6.4.የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ይፋ ማድረግ . . . . . . . . . . . . 19**

**6.5.የዲያስፖራ አባላትን መደገፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19**

**7. የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19**

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የዲያስፖራውን ተሳትፎ የማሳደግና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅማቸውን የማስከበር ሥልጣንና ሀላፊነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሰጠቱ ይታወቃል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም በተሰጠው ሥልጣንና ሀላፊነት መሠረት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላትን ተሳትፎ ለማጎልበትና መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

በዚህም ጅምር እንቅስቃሴ በርካታ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት መዋዕለ ንዋያቸውን ሀገር ውስጥ በማፍሰስ፣ ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር፣ የውጭ ምንዛሬ ወደ ሀገር ውስጥ በመላክ፣ ንግድና ቱሪዝምን በማስፋፋትና፣ የሀገራችንን ገጽታ በመገንባት ረገድ ተጨባጭ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህንም በጎ ጅምሮች በማጎልበት ዲያስፖራውን በሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት በማሳተፍ ራሱንና ሀገሩን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ መቅረጽ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ሆኗል፡፡

በዚህ መሰረት በዲያስፖራው ስራ ዙሪያ የቆዩ መመሪያዎችና አፈፃፀሞችን በዝርዝር በማጥናት፣ ከተለያዩ ጽሁፎችና የተሞክሮ ልውውጥ መድረኮች እንዲሁም የሌሎች አገሮች ጠቃሚ ልምዶችን በግብአትነት በመጠቀምና ከዲያስፖራው የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ይህ የፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የዲያስፖራ ረቂቅ ፖሊሲ በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል የዓለም አቀፍና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ነባራዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ፣ ትርጉም ፣ራዕይ ተልዕኮና ዓላማ እንዲሁም የፖሊሲውን አስፈላጊነት በሚመለከቱ ነጥቦች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ፣ በሁለተኛው ክፍል የፖሊሲው መሠረታዊ መርሆዎችና ዋና ዋና ግቦች ተካተዋል፣ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የፖሊሲው ስትራቴጂዎችና አስፈፃሚ አካላትን የሚያመለክት ነው፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. የዲያስፖራ ተሳትፎ ነባራዊ ሁኔታዎች ቅኝት

### 1.1 የዲያስፖራ ተሳትፎ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

የሰው ልጅ በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ከጀመረ ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ የታሪክ ጸሀፊዎች ከምስራቅ አፍሪካ ተነስቶ ወደ ሌላው የአለም ክፍል የተደረገው የሰዎች እንቅስቃሴ የመጀመሪያው የህዝብ ፍልሰት ነው ይሉታል፡፡ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ገጽታ ያላቸው የሰዎች ፍልሰቶች ተከስተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ ደረጃ የሚደረግ ዝውውር በአንጻራዊነት የቅርብ ጊዜ ታሪክ ያለው ነው፡፡

በተለይ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ግሎባላይዜሽን ከፈጠረው ሁኔታ ጋር በተያያዘ የካፒታል፣ የምርቶች፣ የመረጃና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዝውውር እያደገ መምጣትን ተከትሎ የሰው ልጆች ፍልሰትም በከፍተኛ ደረጃ ሊያድግ ችሏል፡፡ በተለይም ዘመኑ ዕውን ያደረጋቸው ፈጣን፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የመገናኛና የትራንስፖርት አውታሮች ለሰዎች ዝውውር መጨመር የራሳቸውን አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በዓለም ከ200 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ማለትም ከዓለማችን ጠቅላላ ህዝብ 3 ፐርሰንት የሚሆነው ህዝብ ከትውልድ አገሩ ውጭ የሚኖር ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በየዓመቱ የ2.9 ፐርሰንት ዕድገት እንደሚኖረው ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳን ፍልሰት በጦርነት እና መሰል ጉዳዮች አስገዳጅነት የሚሰደዱትን የሚያጠቃልል ቢሆንም አሁን በአብዛኛው እየጨመረ በመምጣት ላይ ያለው ፍልሰት በበለጸጉት አገሮች አሉ ተብሎ ከሚታሰቡ ምቹ ሁኔታዎችና እድሎች በሌላ በኩል ደግሞ በታዳጊ አገሮች ካለው የልማት እንቅስቃሴ ደካማ መሆን እና ሠፊ የስራ ዕድሎች ያለመኖር ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሚከሰት መሆኑ ይስተዋላል፡፡

ፍልሰት በመነሻ አገሮች እና መዳረሻ አገሮች ዘንድ በተለያየ ገፅታ ይታያል፡፡ በአንድ በኩል ፍልሰት የመነሻ አገርን የተማረ ወይም አምራች የሰው ኃይል የሚያሳጣ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ጎጂ ነው የሚል አመለካከት ያለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር የሚገኙ የመነሻ አገር ዜጎች በ remittence፣ በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በኢንቨስትመንት… ወዘተ መስኮች ለትውልድ

ሃገራቸው ልማትና እድገት ከሚያበረክቷቸው በጎ አስተዋጽዎች አንጻር ጠቃሚ ነው በማለት የመስኩ አጥኚዎች ይከራከራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ዜጎች በስደት ላይ ሆነው ለሃገራቸው ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋፅኦ ከሃገር ሳይወጡ ማበርከት ከሚችሉት ጋር ሲነፃፀር ውስን ነው የሚለው ሃሳብ ብዙዎችን የሚያስማማ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ መዳረሻ  አገሮችም ስደት በአንድ በኩል የዜጎቻቸውን የስራ ዕድል ያጣብባል ብለው ሲኮንኑ፣ በተቃራኒው ደግሞ በሰው ሃይል እጥረት የሚያጋጥሟቸውን የስራ ክፍተቶች በመሙላት ረገድ ጠቃሚነቱን ይገልፃሉ፡፡

የሆነው ሆኖ መነሻና መዳረሻ ሃገሮች ፍልሰትን ማቆም የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ የፍልሰት ጎጂ ጎኖችን በመቀነስ በጋራ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መስራት የተሻለ አማራጭ መሆኑን በአለም ዓቀፍ ደረጃ መግባባት ላይ እየተደረሰ ነው፡፡

በመሆኑም ፍልሰትን በትክክለኛ የፖሊሲ አቅጣጫ መምራት ከተቻለ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ተጨማሪ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር በማስገኘትና ድህነትን በመቀነስ እንዲሁም በመዳረሻ አገሮች ደግሞ የሚኖሩ የሰው ሀይል እጥረቶችን በመሙላት የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የራሱ ሚና ያለው መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ::

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳይ በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በክልላዊና  በአለም አቀፍ የትብብር መድረኮች ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሆኗል፡፡ ለዚህም በርካታ አገሮች ዲያስፖራዎቻቸው ባሉበት ሆነው ወይም ተመልሰው በዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በንግድ፣ በቱሪዝም፣ በኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና ተሳትፎ፣ የውጭ ምንዛሪ በማሳደግ፣ በገጽታ ግንባታ፣ለአገራቸው የመልካም ግንኙነት ድልድይ በመሆንና በበጎ አድራጎት ተግባራት በሰፊው የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችሉ መዋቅሮችን በመዘርጋትና ፖሊሲ በመንደፍ ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀደም ብለው ይህን ተግባራዊ ያደረጉ አንዳንድ አገሮች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ውጤቶችን አስመዝግበዋል::

## 1.2. የኢትዮጵያውያ ዲያስፖራ ተሳትፎ ቅኝት

ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና፣ ማህበራዊ ምክንያቶች ትውልድ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ተለያዩ ሀገራት ፈልሰው መኖር ከጀመሩ ዓመታት አስቆጥረዋል፡፡ በአፄ ኃይለስላሴ ሥርዓት ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያውያን ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ሀገሮች በመሄድና በመማር ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ከሞላ ጎደል ሁሉም ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲያገለግሉ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የንጉሱ ስርዓት በአምባገነናዊው ወታደራዊ ደርግ ሲተካ በወቅቱ በውጭ ትምህርት ላይ የነበሩ አብዛኞዎቹ ኢትዮጵያዊያን በያሉበት ሲቀሩ ጥቂት ዜጎች ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል ፡፡ ይሁን እንጂ በሥርዓቱ አምባገነናዊ ባህርይ ምክንያት አገር ውስጥ የነበረው የተማረው የሰው ሃይልም ሆነ በአጎራባች ሀገሮች ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ተስፋ በመቁረጥና አማራጭ በማጣት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አገራቸውን ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ ወደ ሌሎች ቦታዎች የሚሄዱት እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዜጎቻቸው በከፍተኛ ደረጃ በሰሜን አሜሪካን ጥገኝነት ከሚጠይቁ አስር አገራት አንዷ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

የደርግ መንግስት ከተገረሰሰና ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ቢሆን በቀይ ሽብር ከሚፈለጉ ወንጀለኞች ባሻገር ዜጎች ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ለማግኘት፣ በውጭ አገሮች የሚሰጡ የተለያዩ የመኖሪያ ፈቃዶች ተጠቃሚ ለመሆንና የተሻለ ክፍያ የሚያስገኙ የስራ ዕድሎችን ለመፈለግ ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ጠቅላላ ብዛታቸው በግምት ከ2 ሚሊዮን የማያንስ የኢትዮጵያውያ ዲያስፖራ አባላት በሰሜን አሜሪካና፣ አውሮፓ መካከለኛው ምስራቅ አውስትራሊያና አፍሪካ አገሮች ውስጥ እንደሚገኙ የሚገመት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ  የሚገኙት በተነጻጻሪ ከአገር ውስጥ የተሻለ ገቢና የትምህርት ዝግጅት ያላቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡

በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገር ውስጥ በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ፣ ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር፤ ወደ ሀገራቸው የውጭ ምንዛሪ በመላክና ወዘተ ቤተሰቦቻቸውንና አገራቸውን መርዳት ከመጀመራቸውም በላይ የሀገሪቷን ገፅታ በመገንባትና ለሀገራቸው ጥብቅና በመቆም ረገድ አስተዋፅዖ ማበርከት ጀምረዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በመካከለኛው ምስራቅ የተፈጠረውን የጉልበት ስራ ዕድል ለመጠቀም ወደ አካባቢው የተጓዙት ብዛት ያላቸው ያልተማሩና (Unskilled) ጥቂት መለስተኛ ሙያተኞች (Semi-skilled) ለአገርና ለመንግስት ጥሪ ፈጥኖ በመድረስና በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው remittance ወደ ሀገር በመላክ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚደረገው የህገወጥ ሰዎች ዝውውርና የሥራ ስምሪት እያደገ መምጣቱ በአንድ በኩል የዜጎችን መብት በማስጠበቅ ረገድ ውስብስብ ሁኔታዎችን የፈጠረ ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ያለውን ውስብስብ ችግር በሂደት እየፈቱ ካለው ሰፊ ዲያስፖራ የተሻለ ሃገራዊ ጠቀሜታ ማግኘት የሚቻልበት ዕድል ስለመኖሩ አመላካች እየሆነ መጥቷል፡፡

በመካከለኛው ምሥራቅ ከፍተኛ ዲያስፖራ ካለባቸው አገራት አንዷ እስራኤል ስትሆን፤ ቁጥራቸው ከ120 ሺህ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን አይሁዶች በእስራኤል እንደሚገኙ ይገመታል ፡፡ እነዚህም በትውልድ አገራቸው በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ የጀመሩ በመሆኑ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለውን ታሪካዊ ትስስር በማጎልበትና ዲያስፖራውን ይበልጥ ተሳታፊ በማድረግ የተሻለ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ከቅርብ አመታት ወዲህ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ በተማሩና ባልተማሩ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ በመዳረሻ ሀገርነት እየተመረጠች ያለችው ደቡብ አፍሪካ ስትሆን፤ ከባለሙያዎች ፍልሰት አንፃር ደግሞ ቦትስዋናና ኢኳቶሪያል ጊኒ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ከሚኖሩ ዲያስፖራዎች

ጋር የቅርብ ትስስርና የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር እነርሱንና ሀገሪቷን ተጠቃሚ የማድረግ ዕድል ይኖራል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ በመላው አለም የሚገኙ አዲስ ትውልድ (new generation) ዲያስፖራዎችና በጉዲፈቻነት ወደ ምዕራቡ ዓለም እየፈለሱ ያሉ ህፃናት ዲያስፖራዎች ቁጥርም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ እነዚህን አዲስ ትውልድ ወጣቶችና የጉዲፈቻ ልጆች ከትውልድ አገራቸው ባህል፣ ቋንቋ እና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች ጋር ከወዲሁ በማስተሳሰር ለወደፊቱ የሃገሪቱ እሴት እንዲሆኑ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ከፍተኛ ሃገራዊ ጥቅም ማስገኘት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አገራችን በከፍተኛ ደረጃ የሰው ኃይል ወደ ውጭ ከሚፈልሱባት አገሮች አንዷ መሆኗ እሙን ነው፡፡ ይህ በአንድ በኩል በሀገር ውስጥ ያለውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍልሰት በተወሰነ ደረጃ መቀነስ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አስፈላጊነትን የሚያመላክት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ ሃገር ከሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር በሃገር ውስጥ በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት የሚሳተፉበትንና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር አስፈላጊነትን በጉልህ የሚያመለክት ነው፡፡

## 2. የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፖሊሲ አስፈላጊነት

በውጭ የሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት በትውልድ አገራቸው እየተካሄዱ በሚገኙ የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ሂደቶች ላይ በመሳተፍ ራሳቸውንና አገራቸውን መጥቀም እንዲችሉ ዋና ዋና የፖሊሲ ሰነዶችና መመሪያዎች ወጥተው የተለያዩ የማበረታቻ እርምጃዎችም ሲወሰዱ ቆይተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፣

2.1 ............................................................................................................
የዜጎችን በነፃ የመንቀሳቀስ መብት፣ የወሰዱትን የውጭ ዜግነት ከመለሱ የሃገራቸውን የዜግነት መብት መልሰው የማግኘት መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ተግባራዊ መደረጉ፣

2.2 ........................................................................................................

በውጭ አገር የሚገኙ የኢትየጵያ ዜጎች መብትና ጥቅም እንዲከበር የማድረግ ሃላፊነትና ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 254/94 አንቀጽ 25 ቁጥር 10 መሠረት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት መሰጠቱ፣

2.3 ........................................................................................................

የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ ዜጎችን በትውልድ ሀገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 270/94፣

2.4 ........................................................................................................

ለውስጥ ባለሀብቶች እና ለዲያስፖራ ስለተፈቀዱ የሥራ መስኮች የወጣ ደንብ ቁጥር 84/95፣

2.5 ........................................................................................................

ከውጭ በተመጣጣኝ ክፍያ በሃዋላ ገንዘብ የመላክ አገልግሎትን በተመለከተ የወጣ መመሪያ ቁጥር FXD 30/2006፣

2.6 ........................................................................................................

የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱና እንዲንቀሳቀሱ ለመፍቀድ ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 31/98፣

2.7 ........................................................................................................

የዲያስፖራን ጉዳይ የሚከታተል አካል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ መቋቋሙና በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የቅንጅታዊ አሠራር ማነቆዎችን መፍታት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መፈጠራቸው ዋና ዋና ተጠቃሽ እርምጃዎች ናቸው፡፡

እነዚህ እላይ የተጠቀሱት አዋጆችና መመሪያዎች ቢወጡም የዲያስፖራን ጉዳይ ወጥ በሆነ አሰራር ለመምራት የሚያስችል አገራዊ ፖሊሲ ተቀርፆ ዲያስፖራው ከትውልድ አገሩ ጋር በጥብቅ እንዲተሳሰርና ያለውን ዕምቅ ኢኮኖሚያዊና ሙያዊ

አቅም በተሟላና በተቀናጀ መልኩ ሥራ ላይ እንዲያውል የሚያስችል እንቅስቃሴ ተደርጓል ማለት አያስደፍርም፡፡

በመሆኑም ዲያስፖራው በትውልድ ሀገሩ እየተመዘገበ ስላለው የሰላም፣ የልማትና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በቅርበት ተገንዝቦ በተቀናጀ መልኩ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የበኩሉን ሀገራዊ ግዴታ እንዲወጣ ለማድረግ፣ በሚኖርበት ሃገር መብትና ጥቅሙ እንዲጠበቅለት ለመደገፍና በአገር ውስጥ የታዩ የዲያስፖራ ተሳትፎ ማነቆዎችን ለመፍታት ሃገራዊ የዲያስፖራ ፖሊሲ ማዕቀፍ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 3. የዲያስፖራ ተሳትፎ ፖሊሲ ትርጉምና ዓላማ

### 3.1 ትርጉም፡-

**የኢትዮጵያ ዲያስፖራ** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን እና ትውልደ ኢትዮጵያንን ይመለከታል::

**የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፖሊሲ** ማለት በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ዲያስፖራ ተሳትፎ፣ መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሰጡትን አገልግሎቶች፤ በሌላ በኩል አገራችን የዲስፖራውን የእውቀት፣ የፋይናንስ፣ የግንኙነትና ሌሎች አስተዋፅኦዎች ለመጠቀም እንዲያስችላት የሚረዱ ስፋት ያላቸው ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ተግባራት የሚገለፁበት ሰነድ ነው፡፡

### 3.2 የዲያስፖራ ፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማዎች

**3.2.1** የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ከትውልድ ሀገሩ ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር በአገሩ ልማት ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ጠቅሞ ትውልድ አገሩንም በመጥቀም በጋራ ለማደግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ መፍጠርና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ማስከበር ፡፡

## ክፍል ሁለት

## 4. የፖሊሲው መሰረታዊ መርሆዎች

በዲያስፖራው ዘርፍ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸዉ አበይት ጉዳዮች በፖሊሲው ተለይተዋል፡፡ በእነዚህ ላይ ብቃት ያለው ስራ በመስራት የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን አጋርነት ማጎልበት እንደሚቻል ታምኖበታል፡፡ ይህ አጋርነት ሁሉም ወገኖች በሚጋሩት አገራዊ ጥቅም ላይ የሚመሰረትና በአገሪቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚመራ በመሆኑ ቀጥሎ በተቀመጡትና በብሄራዊ ጥቅም ዙሪያ መታየት ባለባቸው የአጋርነት መሰረተ-ሃሳቦች ላይ ግልጽነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

### 4.1 ሴክተር አቀፋዊነት (A Sector Wide Approach)

የዳያስፖራ ጉዳይ በአንድ ወይም በራሱ ሴክተር ብቻ ያልታጠረና ከብዙ ሴክተሮች ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ፖሊሲውን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት ከሌሎች ተጓዳኝ ሴክተሮች እንቅስቃሴ ጋር ተጣጥመው መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.2 ውጤታማነት (A Safe Policy)

የጥረታችን ሁሉ የመጨረሻ ግብ ድህነትን ማስወገድ እስከሆነ ድረስ ይህ የዳያስፖራ ፖሊሲ ድህነትን ለማስወገድ የሚደረገውን ትግል ለማሳካት ወይም በውጤት ለማጠናቀቅ በሚያስችል መልኩ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

### 4.3 የሃብት አጠቃቀም

የዳያስፖራ ፖሊሲውን ለማስፈጸም የምንከተላቸው ስትራተጂዎች በሙሉ ካለን ውስን ሃብትና ንብረት (Resources) አቅም ጋር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የፖሊሲው ተፈጻሚነት ከሃገሪቱ የሃብትና ንብረት አጠቃቀም ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ የሚከናወን ይሆናል፡፡

### 4.4 ተደጋጋፊነት (Complementarily)

የዳያስፖራ ፖሊሲው ከሌሎች ብሄራዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎችና ፕሮግራሞች ( የድህነት ቅነሳ (PRS)፣ ዓለምአቀፍ የልማት ግቦች (MDG)... ) አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋግፎ እንደሚሄድ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

## 5. የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች

### 5.1 በውጭ የሚኖሩ ዜጎችን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ:-

5.1.1 የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ምዝገባ ስርዓት ይዘረጋል

5.1.2 በሚስዮኖች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ዲያስፖራው በሚገባ እንዲያውቃቸው ለማድረግ የሚያስችሉ ወቅታዊ አገራዊ መረጃዎችንና ፖሊሲዎችን የማስተዋወቅ ስራዎች ይካሄዳሉ፣

5.1.3 በውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ዜጎች በአደጋ ጊዜ ማንነታቸውን በመለየት ድጋፍ ለመስጠትና በአገራቸው ለሚኖራቸው የልማት ተሳትፎ እንዲያመች በሚስዮኖቻችን በኩል የቆንስላ መታወቂያ ካርድ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ከወዳጅ አገሮች ጋር በመደራደር መታወቂያ ካርዱን ለያዙና ስራ ላገኙ ወገኖች ዕውቅና እንዲሰጡ ጥረት ይደረጋል፡፡

5.1.4 የኢትዮጵያ ሚስዮኖች በሌሉባቸውና በርካታ ዜጎቻችን በሚኖሩባቸው አገሮች የክብር ቆንስላ የሚሾምበት ወይም ከኮሙዮኒቲ ማህበራት ጋር በመተባበር ዜጐች አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያሰፋል፣ የተንቀሳቃሽ የአገልግሎት ኣሰራርን ያተጋል፡፡

5.1.5 ዜጎች በሚኖሩባቸው አገሮች በሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎችና አለመረጋጋቶች ሳቢያ ከሚፈጠሩ ችግሮች ለመታደግ የሚደረጉ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

5.1.6 ሠራተኛንና አሰሪን የሚያገናኙ ኤጀንሲዎች ከሚሲዮኖች ጋር ግንኙነት ኖሯቸው የላኳቸውንና የተቀበሏቸውን ሰራተኞች በሚመለከት በሚሲዮኖች በኩል ጥብቅ ክትትል ይደረጋል፣ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖርና ለውጤታማነቱ በሚሲዮኖች፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መካከል በኔትወርክ ግንኙነት ይፈጠራል፡፡

5.1.7 ዜጐች በኮሚኒቲዎች በኩል የሚያደርጉትን ዕገዛ በማጠናከር የኮሙዩኒቲ ማህበራት (Welfare Associations) እንዲስፋፉና ከፍተኛ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የእርስ በርስ መደጋገፍ እንዲጠናከር ያተጋል፡፡ ከኮሚዩኒቲው ጋር በመተባበር ለአጭር ጊዜ የሚቆዩበት መጠለያ ማቋቋምን በሚመለከት በጥናት ይመልሳል፡፡

5.1.8 የኮሚኒቲ ማህበራት ከFoundations፣ ከሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተው መስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ያተጋል፣

5.1.9 ዜጎቻችን በብዛት ለስራ ከተሰማሩባቸው የመካከለኛው ምስራቅና ባህረ-ሰላጤ አገሮች ጋር የሥራ ስምምነት (Labour Agreement) ለመፈራረም እየተደረገ ያለውን ጥረት ያጠናክራል::

## 5.2. የኢንቨስትመንት፣ የንግድና ቱሪዝም ተሳትፎን ማጐልበት

### 5.2.1. ኢንቨስትመንት:-

5.2.1.1 ውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ወቅታዊ የኢንቨስትመንት መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር በዲስፖራው ላይ ያተኮረ ፕሮሞሽን እንዲያካሂዱ ይደረጋል፣

5.2.1.2 ማንኛውም በውጭ የሚኖር የዲያስፖራ አባል አግባብነት ባላቸው የኢንቨስትመንት መስኮች መዋዕለ ንዋዩን በቀጥታ ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና ኢንቨስት እንዲያደርግ ይበረታታል፣

5.2.1.3 የፌዴራልና የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤቶችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዲያስፖራው በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት የሚያደርጋቸውን ጥረቶችና የሚያቀርባቸውን ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነት እንዲያበረታቱና እንዲተባበሩ ይደረጋል፣

5.2.1.4 የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት ውጣ ውረዶችን ለመፍታትና ዲያስፖራውን በቀጥታ ኢንቨስትመንት ውስጥ ለማስገባት የዲያስፖራ ኢንዱስትሪ ዞኖች (DIZs) ተከልለው እንዲዘጋጁ ይደረጋል፣

5.2.1.5 ኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች በትውልድ አገራቸው በኢንቨስትመንት መስክ ለመሳተፍ ከሚኖሩባቸው ሀገሮች ብድር ወይም የብድር ዋስትና ዕድል ሲያገኙ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርግላቸዋል፣

5.2.1.6 ዲያስፖራው የቅድሚያ ትኩረት በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች በግል/በጋራ ኢንቨስት እንዲያደርጉ መንግስት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

5.2.1.7 በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ትውልድ አገራቸው ውስጥ ለሚሰሩት ስራ የሚያቋቁሙትን የንግድ አክሲዮን በየአከባቢያቸው በሚገኙ ሚሲዮኖች አማካይነት ሕጋዊ በማድረግ በአገር ውስጥ ለማስመዝገብ የሚቻልበት አሠራር ይዘረጋል፡፡

**5.2.2. ንግድና ቱሪዝም፡-**

የዲያስፖራ አባላት ንግድን በሚያስፋፉ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ በክህሎታቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይበረታታሉ፣

5.2.2.1 ዲያስፖራው በአገር ውስጥ ለሚገኙ አስመጪና ላኪ እንዲሁም አስጎብኚ ድርጅቶች በገበያ ኢንተለጀንስ ዘርፍ፣ በአገናኝነትና በሽያጭ ሠራተኛነት የዳበረ ልምዱን በማካፈል ራሱንና ድርጅቶችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ይበረታታል፣

5.2.2.2 ዲያስፖራው ለሀገራችን ዋና ዋና ምርቶች niche market በማፈላለግ ራሱንና ላኪዎቹን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት ይደረጋል፣

5.2.2.3 ከአገራችን ምርቶች በተለይም ባህላዊ የዕደ ጥበብ ውጤቶች መካከል የማህበረሰቡ አባላት በብዛት በሚኖሩባቸው አገሮች ገበያ ሊያገኙ የሚችሉትን በመለየት፣ ምርቶቹን ለሚያመርቱና ለሚያከፋፍሉ ልዩ የፕሮሞሽን ፓኬጅ ይዘጋጃል፣ የብድር አገልግሎትም ይመቻቻል፣

5.2.2.4 በውጭ የሚኖሩ የዲያስፖራ አባላትና ለአጭር ጊዜ የትምህርትና የስልጠና ቆይታ ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን ቱሪዝምን በማስፋፋት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፣

5.2.2.5 ኢትዮጵያዊያን ህጻናትን በጉዲፈቻ ወስደው የሚያሳድጉ ቤተሰቦችና ታዳጊ ህፃናት የኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦችና ቦታዎችን እንዲጎበኙና የቱሪዝም ሀብቶቻችንን እንዲያስተዋውቁ የጉብኝት ፓኬጅ ይዘጋጃል።

## 5.3. የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፡-

5.3.1 ዲያስፖራው አግባብነት ባላቸው የመንግስት መ/ቤቶች፣ የትምህርትና የጤና ተቋማት ወዘተ ውስጥ በሙያቸውና በልምዳቸው በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ለማገልገል ከጠየቁ ባለው የመንግሥት መመሪያ መሠረት የሥራ ዕድል እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፣

5.3.2 በጡረታ የተሰናበቱ ከፍተኛ የትምህርት ባለሙያ የሆኑ የዲያስፖራ አባላት በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ የሚያስተምሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

5.3.3 በውጭ ሀገር የነበራቸውን ከፍተኛ ደሞወዝ ቀንሰው በዕውቀታቸው አገራቸውን ለማገልገል ለሚመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች አስፈላጊው ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፣

5.3.4 መንግስት ትኩረት በሚሰጣቸው የምርምር መስኮች ውስጥ ልዩ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ጥናቶችን እንዲያካሂዱ ይበረታታሉ፣

5.3.5 ወደ አገራቸው ገብተው ልዩ ክህሎት በሚጠይቁ (የትምህርት፣ የጤና፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ...) መስኮች በመስራት ላይ ያሉ የዳያስፖራ አባላትን በተጠናከረ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል የዕውቀት ፓርክ (Knowledge Park) የሚቋቋምበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

5.3.6 በውጭ ሀገር በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ወጣት ዲያስፖራዎች በአገር ውስጥ በሚገኙ የመንግስትና የግል ተቋማት ውስጥ የሥራ ልምምድ (Internship) የሚያደርጉበት ፕሮግራም ይመቻቻል፣

5.3.7 ወደ አገር ቤት መጥተው ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ለማስተላለፍ ፍላጎት ያላቸውን የነፃ አገልግሎት ሰጪ(volunteer) ወጣቶችን ያበረታታል፣

5.3.8 በመካከለኛው ምሥራቅና በጎረቤት ሀገሮች የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ከፍተኛ ትምህርታቸውን በተልዕኮ የሚማሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ኮሚኒቲ ት/ቤቶችም እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣

5.3.9 በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ በዕርዳታ የተገኙ ማቴርያሎች በአፋጣኝ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበትና ጥቀም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ይመቻቻል::

## 5.4. የውጭ ምንዛሪ ማስገቢያ መንገዶችና ተሣትፎን ማሳደግ

5.4.1 ወደ አገር ቤት ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች በውጭ ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪና በአገልግሎት ያገኙትን የጡረታ አበል ገቢያቸውን ወደ አገር ቤት ይዘው እንዲመጡ የሚያበረታታ አሰራር ይዘረጋል፣

5.4.2 በውጭ የሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች (ለቤተሰብ፣ ለኢንቨስትመንት ወዘተ) ወደ ሀገር የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ በህጋዊ መንገድ እንዲሆን የሚያበረታታ አሰራር ይዘረጋል፣

5.4.3 ሚሲዮኖቻችን ከሀገር ውስጥ የኢትዮጵያ ባንኮች ጋር በመተባበር በየተወከሉባቸው አገሮች በመደበኛ መንገድ ገንዘብ ወደ አገር ቤት የማስተላለፍ አገልግሎት ከሚሰጡ ባንኮች/ድርጅቶች ጋር በመደራደር ዲያስፖራው የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኝ ጥረት ይደረጋል፣

5.4.4 ዲያስፖራው በትውልድ አገሩ ለሚያካሂዳቸው ኢንቨስትመንቶችና የልማት ተግባራት ከአገር ውስጥ ባንኮች ለወሰዱት የብር ብድር እንዲሁም ለሚገዟቸው የፌደራልና የክልል ቦንዶች በውጭ ምንዛሪ የሚከፍሉበት አሰራር ይቀየሳል፡፡

## 5.5. ባህላዊ እሴቶችን ማዳበርና ገጽታ ግንባታን ማትጋት

5.5.1 በርካታ የኮሚኒቲ ማህበራት ባሉባቸው አገሮች የባህል ማዕከላትን በመክፈት ዲያስፖራው ከሀገሩ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ጋር እንዲተሳሰር ይደረጋል፣

5.5.2 የዲያስፖራ አባላት በትውልድ አካባቢያቸው የባህል ማዕከላትና ሙዚየሞችን በመገንባት ታሪካቸውንና ባህላቸውን እንዲጠብቅ ይበረታታሉ፣ አስፈላጊው ድጋፍም ይሰጣል፣

5.5.3 የዲያስፖራ አባላት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ለሚያዘጋጁቸው የባህልና የኪነት ትርዒቶች እንዲሁም የስፖርት በዓላት አስፈላጊው ማበረታቻና ድጋፍ ይሰጣቸዋል፣

5.5.4 ወጣት ዲያስፖራዎች ከትውልድ ሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ለማጠናከር የተደራጀ የአገርህን ዕወቅ ፕሮግራም (Know Ethiopia Programme -**KEP**) ይቀረፃል : :

## 5.6 በዲሞክራሲያዊ ሂደት የሚኖረውን ተሳትፎ ማሳደግ

5.6.1 በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊን በምርጫ እንዲካፈሉ የምርጫ ኮሚሽን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የሎጀስቲክስ ችግሩን ከዲያስፖራው ጋር በመተባበር የሚፈታበትን መንገድ ያጠናል፣

5.6.2 ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ በምርጫ ወቅት በተደራጀ መልኩ በታዛቢነት የሚሳተፍበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

5.6.3 የሌላ አገር ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸውና ኑሯቸው በወሳኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ የሆኑትን ዜጎች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በሚኖሩበት አካባቢ በምርጫ ለመሳተፍ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ : :

## 5.7 የግብረ ሰናይና የልማት ማህበራትን ማትጋት

5.7.1 በዲያስፖራ የሚደረግ የግብረ ሰናይ መዋጮ ከማንኛውም ሀይማኖታዊና የፓለቲካ ግንኙነቶች የተላቀቀ መሆኑን በማረጋገጥና መልክ ባለው መንገድ እንዲገባ በማድረግ ይስተናገዳል፣

5.7.2 የተደራጁ በጎ ፈቃደኞችን አስተዋጽኦ በማትጋት ተደራጅተው የነፃ አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ይዘረጋል፣

**5.7.3** ዲያስፖራው በአገሩ ለሚያከናውናቸው የግብረ-ሰናይ ስራዎች ከሚኖርባቸው የበለጸጉ አገሮች ለሚያመጣቸው ቁሳቁሶች የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ያገናዘበና ተመጣጣኝ የሆነ የታክስ ማበረታቻ የሚደረግበት የአሰራር ሁኔታ ይጎለብታል፣

**5.7.4** በልማት ማህበራት ዙርያ ከውጭ የሚደረገውን የልማት መዋጮ ማሳደግ የሚያስችልና ገንዘቡን አግባብ ባለው መንገድ በፍጥነት ወደ ልማት ማዋል የሚያስችል አሰራር ይጎለብታል : :

**5.8** የኢትዮጵያን ገጽታ በሚያስጠብቁ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ

**5.8.1** የኢትዮጵያን ምርቶች በሚያስተዋውቁ በውጭ አገራት በሚዘጋጁ መድረኮች
እንዲሳተፉ ማድረግ፣

**5.8.2** ወቅታዊ አገራዊ ሁኔታዎችን እንዲከታተሉ በማድረግ የኢትዮጵያን ብሄራዊ
ጥቅምና ገጽታ በሚያስጠብቁ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ፡፡

# ክፍል ሦስት

# 6. የፖሊሲው ስትራቴጂዎች

## 6.1 አስተማማኝ የመረጃ ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት

### 6.1.1 የመረጃ አገልግሎትን ማስፋት

**6.1.1.1** በዲያስፖራ ላይ ያተኮረ የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ስርጭትን ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረ የዲያስፖራ መረጃ ቋት (data base) ና ድረ-ገጽ (web site) እንዲደራጅ ይደረጋል፣

**6.1.1.2** መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስና (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ዌብሳይት፣ ኢ-ሜል ወዘተ) በህትመት ውጤቶች አማካይነት ለዲያስፖራው የሚደርሱበት ስርዓት ይዘረጋል፣

**6.1.1.3** በሀገር ውስጥና በርካታ የዲያስፖራ አባላት በሚገኙባቸው ሀገራት የስብሰባ መድረኮችን፣ ሲምፖዚየሞችንና ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት ዲያስፖራውን ለማገናኘትና ለማወያየት ትኩረት ይደረጋል፡፡

**6.1.1.4** ዲያስፖራው በሀገር ውስጥ ስለሚካሄዱ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደቶች የተሟላ ግንዛቤ እንዲጨብጥ የኮሚዩኒቲ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፣

## 6.1.2. ቋሚ የመረጃ ልውውጥ መድረኮችን መፍጠር

### 6.1.2.1 በአገር ቤት ቋሚ የዳያስፖራ ቀን በዓል አከባበር (Homecoming Event)

**6.1.2.1.1.1** በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደረግ የዲያስፖራ ቀን በአገር ቤት በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል፣ በተጨማሪም በርካታ የዲያስፖራ አባላት በሚመጡባቸው አመታዊ በዓላት አነስተኛ መድረኮች ይዘጋጃሉ፣

6.1.2.1.1.2 ክልል አቀፍ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ክልሎችም ተወላጆቻቸውን የሚያሳትፉበት ተጓዳኝ (BACk To BACk) መድረኮች ፣ ከዲያስፖራው ጋር ተያያዥነት ያለው ተግባር የሚያከናውኑና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ፣ ቢዝነሶችና ሙያተኞች በአገር ውስጥ ከሚገኙ አቻዎቻቸውና ተቋማት ጋር ግንኙነት እና ትስስር የሚፈጥሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

### 6.1.2.2 በውጭ ከዳያስፖራ ጋር የሚካሄዱ የግንኙነት መድረኮች (Outreach Programmes)

6.1.2.2.1 መንግስት ከዲያስፖራው ጋር በውጭ የሚያካሂዳቸው መድረኮች በታቀደና ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ይሆናሉ፣

6.1.2.2.2 በተለያዩ ክፍለ-ዓለማት የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ማህበራዊ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩባቸው አመታዊ ፌስቲቫሎች እንዲያዘጋጁ አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 6.2. ለዳያስፖራው ተሳትፎ ዕውቅና መስጠት (Award and Recognition)

**6.2.1** ለትውልድ አገራቸው ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ግለሰቦችና ማህበራት በፌዴራል እና በክልል መንግስታት ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች የሚሸለሙበት አሰራር ይዘረጋል፣

## 6.3. የተደራጀ ተሳትፎን ማትጋት

### 6.3.1. ያሉትን ማህበራት ማጠናከር አዳዲስ እንዲፈጠሩ ማገዝ

**6.3.1.1** የተለያዩ (የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሙያ፣የልማት፣የማህበረሰብ ወዘተ) የዲያስፖራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ይበረታታሉ፣ የተቋቋሙትም የሚጠናከሩበት ስልት ይቀየሳል፣

**6.3.1.2.1** የብሄራዊ የጋራ ይሁንታ መሰረተ-ሃሳብን በሚገባ በማስተዋወቅ የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች በያሉበት የመሰረቷቸው ማህበራት መረጃዎች በአግባቡ ይያዛሉ፣ ሌሎች አዳዲስ ማህበራት እንዲመሰረቱ ይበረታታሉ፣ በተደራጀ መልኩ አገራቸውን እንዲደግፉ ለማድረግ የሚፈልጉትን ድጋፍና ሊያበረክቱ የሚፈልጉትን አስተዋፅኦ በአግባቡ በመለየት ድጋፍ ይሰጣል፣

**6.3.1.3** የዲያስፖራ የሙያተኞች፣ የተማሪዎች፣ የሴቶች፣ ወዘተ... ማህበራት መረጃ መረብ እንዲገናኙ እርስ በእርሳቸው እንዲተዋወቁና ልምድ እንዲለዋወጡ ፣ዓለም አቀፋዊ ማህበራትን ለመመስረት International Network እንዲፈጥሩ በአገር ቤት ካሉ ተመሳሳይ ማህበራት ጋር እንዲተዋወቁ የሚያስችሉ ስራዎች ይከናወናሉ፣

**6.3.1.2.2** ተመላሾች በአገርቤት ተደራጅተው ድምፃቸውን እንዲያሰሙና አዳዲስ ተመላሾችን በተለያዩ ዘርፎች እንዲያግዙ ድጋፍ ይሰጣል፣

## 6.3.2. ለወጣት ዲያስፖራዎች የተደራጀ ተሳትፎ ልዩ ትኩረት ይሰጣል

**6.3.2.1** በውጭ በተለያየ መልክ ተደራጅተው የሚገኙ ወጣቶችን መረጃ በመያዝ በአካልና በኤሎትሮኒክ ሚዲያ አማካኝነት የተጠናከረ ግንኙነት ይመሰረታል፣ አዳዲስ የወጣትና የተማሪዎች ማህበራት እንዲደራጁ ድጋፍ ይደረጋል፣ ዓለም አቀፍ ማህበራት እንዲጠናከሩ ያተጋል፣

**6.3.2.2** በውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ያሉ ወጣቶች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበት ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ የኢትዮጵያን የባህል፣ የስነ-ጽሁፍ፣ የኪነ-ጥበብና ኪነጥበባዊና የስፖርት ዝጅቶች በየዓመቱ እንዲዘጋጁ ያበረታታል፣ ወጣቱ ተደራጅቶ ዋና ተዋናይ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

**6.3.2.3** በውጭ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በሚገኙባቸው የመንግስትና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመገኘት በአገር ቤት ያሉት እድሎች በስፋት ይተዋወቃሉ፣ በስራ ላይ የሚገኙ ሌሎች ወጣት ፕሮፌሽናሎች በተመለከተም ተመሳሳይ ሰሚናሮች እንዲካሄዱ ይመቻቻል፣

**6.3.2.4** የአገራችንን የልማት ስትራቴጂ ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ሴሚናሮችን፣ ወጣት የዳያስፖራ አባላት ያገራቸውን ባህልና ታሪክ እንዲያውቁ የሚያስችሉ ኮርሶች በአገር ውስጥና በውጭ እንዲሰጡ ይደረጋል፣

**6.3.2.5** ከአፍሪካ ህብረት ፕሮግራም ጋር በማጣጣም ከአፍሪካ ወጣቶች የዳያስፖራ እንቅስቃሴ ጋር እንዲቆራኙ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 6.4. የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ

የትውልድ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ ካርድን ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስርና ተሳትፎ የሚያሰፋና የሚያሳድግ ዋነኛና ቋሚ መሳሪያ ለማድረግ በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የመታወቂያ ካርዱ ተጠቃሚዎችን የማስፋትና የመታወቂያ ካርዱን ጥራት የማሻሻል ስራ ለማከናወን በመታወቂያ ካርዱ ዙሪያ መፍትሄ ላላገኙ ጉዳዮች የተጠና መልስ ይሰጣል ፡፡

## 6.5 የዲያሰፖራ አባላትን መደገፍ

**6.5.1** ጠቅልለው ወደ ትውልድ ሀገራቸው የሚመለሱ የዲያስፖራ አባላት በመንግስት መመሪያ መሠረት የቀረጥ ነጻና ቅነሳ ዕድል የሚያገኙበት በጥናት ላይ የተመሰረተ ሥርዓት ይዘረጋል፣

**6.5.2** የዲያስፖራ አባላት በግልና በማህበር ተደራጅተው በክልሎች ፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የመኖሪያ ቤት የሚያገኙበት ሁኔታ በጥናት ላይ በተመሰረተ መልኩ አሰራር ይዘረጋለታል፣

**6.5.3** በተለያዩ የሙያ መስኮች በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ማገልገል ለሚፈልጉ የዲያስፖራ አባላት መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 7. የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት

7.1 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የዲያስፖራ ፖሊሲውን አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣

7.2 የተለያዩ የመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት የሚወከሉበት የዲያስፖራ ብሔራዊ ካውንስል ይቋቋማል፣

7.3 የክልል የዲያስፖራ ጽ/ቤቶች የየክልሎቻቸውን የዲያስፖራ ተሳትፎ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የቅንጅት መድረክ ይኖራቸዋል፣

7.4 በአገር ቤት በተለያዩ መስኮች ከሚሳተፉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት የተውጣጣ አማካሪ ካውንስል ይቋቋማል ፤ ተመሳሳይ አማካሪ ካውንስል በሚሲዮኖች ዙሪያም ይቋቋማል፣

7.5 ስራዎችን በቅንጅት መምራት እንዲቻል በውጭ ጉዳይ የሚመራ የክልሎች የዳያስፖራ ጽ/ቤቶች የጋራ መድረክ ይዋቀራል፣ ቀጣይነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው ይደረጋል፣

7.6 በአገር ውስጥ በዲያስፖራ ዙርያ የተደራጁ ማህበራት እርስ በርሳቸውና ከመስሪያ ቤቱ ጋር ቋሚ ግንኙነት የሚመሠረቱበት አሠራር ይዘረጋል፡፡